

በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከጁን 1-30/2026 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

# እና

# ከጁላይ 1-31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ

# እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2026

አዲስ አበባ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


## 1.1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፈው የጁን ወር ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች፤ በተለይም በመጀመሪያዎቹ እና በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ በልግ ዋነኛና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛዉና ሰሜን የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠሩት ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ መካከለኛ እና የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ20 ሚ.ሜ በላይ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ሀዋሳ 21.5፣ 21.3፣ ባህርዳር 56.4፣ ቢሾፍቱ 20፣ ጎንደር 24፣ ጎሬ 26.7፣ 26.1፣ ጅማ 23.7፣ መቀሌ 25.9፣ ነቀምት 21.1፣ 24.7፣ 39.3፣ 46.5፣ 21.4፣ 54.7፣ 27.7፣ አዴት 30፣ 33፣ 43.8፣ አድዋ 22.4፣ አይራ 24፣ 23.8፣ 28.4፣ 23.4፣ 29.2፣ 33.5፣ 46፣ አንግር ጉትን 35.6፣ 46.4፣ 32.4፣ 30.4፣ አርጆ 32.8፣ 24.5፣ 26.4፣ 34.2፣ 42.2፣ 24፣ አሶሳ 26.4፣ 22.8፣ 25.6፣ አይከል 20.1፣ ብላቴ 33.8፣ በደሌ 31.8፣ 39.6፣ ቦሬ 29.9፣ ቡለን 30፣ 23.4፣ ቡሬ 30.6፣ 22.2፣ 58.8፣ 30፣ 37፣ 38፣ 37.8፣ 41.5፣ ቡሂ 28.5፣ ቻግኒ 40.1፣ 38.4፣ 22.9፣ 26.8፣ ጨዋቃ 32፣ 40፣ 22፣ 30፣ 25፣ ጭራ 21.5፣ 30.5፣ 42.3፣ ደባርቅ 20.2፣ ደብረብርሃን 29.8፣ ደምቢ ዶሎ 32.5፣ 31.2፣ 31፣ 28.8፣ 25.5፣ 27.2፣ ዲላ 20.4፣ ሊጃጂ 20.8፣ ፉኝዶ 32፣ 27.5፣ ጋምቤላ 38.2፣ 20.8፣ 66፣ ጋቲራ 21.7፣ 23.8፣ ገለምሶ 24፣ ጊዳ አያና 33.3፣ 35.8፣ 24.9፣ ጊምቢ 37.7፣ 27.7፣ 45.1፣ 26፣ 39፣ እምድብር 22.2፣ ሊሙገነት 27.3፣ 22.8፣ ማሻ 20.4፣ 30.6፣ 50.2፣ 20.6፣ 122.4፣ መተማ 31.2፣ 55.2፣ ሞጣ 20.6፣ ማንኩሽ 26.2፣ አዳማ 23፣ ነጆ 31.9፣ 79.3፣ 35.4፣ 39.4፣ ፓዌ 33.2፣ ሳዉላ 51.2፣ ሻሁራ 32.9፣ 23.9፣ ሻምቡ 27.9፣ ሸርቆሌ 31.7፣ ሾላ ገበያ 32.7፣ ቴፒ 20.2፣ 21.3፣ ወራቤ 20.3፣ አቦምሪንጋ 91.5፣ 21.4፣ 22፣ አዲስ ዘመን 26.6፣ አሺ 32፣ 24፣ 24፣ እንዳባጉና 23.6፣ መንደር7 27.9፣ ጎሮበቄሳ 23፣ ጎብየሬ 70.8፣ ቅዳሜገበያ 27.4፣ ቀርሳ(ሶማሌ) 27.6፣ አሮሬሳ 20.6፣ አንኮበር 25፣ አሺ 28፣ 30፣ 38፣ 24፣ ኦንጋ 24.5፣ 22፣ 20.7፣ መንደር11 94.5፣ ዉልበረግ 24.2፣ 31.4 ኮሶበር 24.2፣ 36.1፣ 22.8፣ ኩሚ 37.7፣ ሼንዲ 28.5፣ 26.5፣ 31.5፣ ትንሹ ሜጢ 58.3፣ መንደር13 34፣ 22፣ 36.4፣ 28.2፣ እንዲሁም ይርባ ዲባንቾ 33.3፣ ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል። በአጠቃላይ ባለፈው የጁን ወር በ40 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

በሆኑ የምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብና የምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 51.2-122.4 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በምዕራብ ሸዋ አቡና ግንደበረት፣ ግንደበረት እና ሆለታ እና በማዕከላዊ ኢትየጵያ ወልቂጤ በረዶ ቀላቅሎ የዝናብ ዝናብ በሰብል እና በንብርት ላይ ጉዳት አድርሷል፡ ፡





ምስል1: ከጁን 1 እስከ 30/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው ስፍራዎች


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ባለፈዉ የጁን ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ጉጂ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል ጥቂት የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ትግራ ዞኖች፣ አዊ፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከንባታ፣ የም ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ እና ጎፋ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ41-350 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ6-25 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡


ባለፈዉ የጁን ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ የምስራቅ ሸዋ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብና መካከለኛዉ ጎንደር፣ በህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ የሰሜን ጎጃም ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የሰሜን ምዕራብ ትግራይ ዞኖ፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ አሶሳ፣ መተከል፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል  (ካርታ 3) ፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


### 1.2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁን ወር በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው የመኸር ሰብል አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የእርጥበት መጠኑ እየተስፋፋ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ እየተሻሻለ የመጣበትና ሁሉንም ያዳረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበረ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከጁን ጀምሮ የዘር ጊዜና የማሳ ዝግጅት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በወቅቱ ለመዝራት አመቺ ሁኔታ የፈጠረ ሲሆን፤ ዘግይተዉ ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከሟሟላት አንፃር የጎላ ጠቀሜታ ነበረው። በተጨማሪም ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች በተገቢዉ ሁኔታ እድገታቸዉን እንዲቀጥሉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ በተለይም በምዕራብ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት የነበረ ቢሆንም፤ በግብርናዉ አንቅስቃሴ ላይ ያደረሰዉ የጎላ ጉዳት አልነበረም፡፡ በአንጻሩ ግን በምስራቅ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው እርጥበት አነስተኛ ቢሆንም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው (ካርታ 4)፡፡


### 1.3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2026 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳልፈነው የጁን ወር በአብዛኛው ባሮ አኮቦ፣ አባይ፣ በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ተከዜ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ፣ አዋሽ፣ አይሻ እንዲሁም የኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ በተፋሰሶችና ንዑስ ተፋሰሶች ውስጥ ያለውን የውሃ ክምችት በማሻሻል ወደ ግድቦችኛ የውሃ መያዣዎች የሚገባውን የውሃ መጠን ከመጨመር አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው። በሌላ በኩል የተቀሩት በአብዛኛው አፋር ደናክል፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን በታችኛው አዋሽ እንዲሁም በላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ ስር ቆይተው ነበር (ካርታ 5)።

Ethiopian Meteorology Institute




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ ወቅታዊው የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጎራባች የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር ውስጥ የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳርሳል፡፡ በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ወር የክረምት ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ እና እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የተሻለ ዝናብ መጠንና ስርጭት ይስተዋላል። በወሩ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ ስፍራዎች ላይ ከ200-500 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ18-27 ቀናት ያህል ይዘንባል። በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን ከ60-200ሚ.ሜ የሚደረስ ዝናብ ከ6-21 ቀናት ያህል ይዘንባል፡፡ ከክረምት ወቅት የዝናብ ድርሻ አኳያ በጁላይ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከ30 እስከ 50% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ።


## 2.1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በጁላይ የመጀመሪያው አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ ይበልጥ እየተስፋፋና


እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆንና፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ደግሞ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ ከባድ (ከ1-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በውሃ አካላትና አከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6) ፡፡


በጁላይ የመጀመሪያው አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በአፋር ክልል፣ በምስራቅ አማራ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሊይ ከ32 እስከ 41 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-10 /2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-10 /2026, የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-10 /2026, የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ጥቂት የምስራቅ ቦረና ዞን | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| አማራ | የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እናደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ፣ ፋፈን፣ ኤረር፣ ነጎብ፣ ዳዋ እና ሊበን ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |


Ethiopian Meteorology Institute

## 2.2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ


በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ወር በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ እና እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ነጎድጓዳማና በረዶ አዘል ዝናብ ይኖራል፡፡ በተጨማሪም የዝናቡ ጥንካሬም ለረጅም ሰዓታት ያለማቋረጥ የሚዘንብበት ወር ነው፡፡

በመጪው የጁላይ ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት ላይ የተሻለ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ

በመነሳት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ እንደሚሆን የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንዳንድ አካባቢዎችም ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ደመናዎች ላይ በመነሳት ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር የአሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 9 እና 10)፡ ፡በአጠቃላይ በሚቀጥለው የጁላይ ወር የሚጠበቀውን የአየር ጠባይ ትንበያን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና የሚገኘውን የዝናብ መጠንና ስርጭት በአግባቡ በመጠቀምና በማሳባሰብ በዚህ ወቅት የሚካሄደውን የግብርና እንቅስቃሴ ሥራዎችን ከባለሙያዎች ጋር በመመካከር ማከናወን ያስፈልጋል፡፡




ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የዝናብ መጠን ከረጅም ግዜ አማካይ ሲነፃፀር




ካርታ 10 እ.ኤ.አ. እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

### 2.3 እ.አ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የጁላይ ወር በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሁለት ሳምንታት በአንዳንድ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉና የደቡብም ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን የሚያሻሽል ከመሆኑ አንፃር ዘር ለመዝራት፣ አስቀድመው የተዘሩና

በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች እድገት፣ ለቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ እና በመደበኛ ባህሪያቸው በእርጥበት መብዛት በሚታወቁ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ከመጠን በላይ ሊሆን ስለሚችል በዚህም ምክንያት ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ከእርጥበት መብዛት ጋር የአረም መከሰትና የሰብል ተባይ መፈጠር ሊኖር ስለሚችል ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ የቅድመ ጥንቃቄ ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የማደበሪያና ጸረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀም የዝናቡን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል የሚጠበቀው እርጥበት በልግ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች በደርሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ በመካከል በሚገኙ ደረቅ ቀናቶች  የሰብል ስብሰባን ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## 2.4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2026 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ የጁላይ ወር የሚጠበቀው የገጸ ምድር የውሃ ሽፋን በአብዛኛው ተከዜ፣ መረብ ጋሽ፣ አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው እና የመካከለኛ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም የአዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከመካከላኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። በተጨማሪም በላይኛው እና በመካከለኛው ገናሌ ዳዋ፣ ዋቢ ሸበሌ እንዲሁም በኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ መካከለኛ የሚደርስ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይጠበቃል።  ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት በሚጠበቅባቸውና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ የጎርፍ ክስተት፣ የመሬት መንሸራተት እና የወንዞች ሙላት ሊያስከትል ስለሚችል ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር አካባቢዎች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ቅድመ ጥንቃቄ ስራዎችን ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

Ethiopian Meteorology Institute